

gage

**የስርዓተ ፆታና ታዳጊነት፡ አለማቀፋዊ መረጃ**

## የጌጅ አጭር መግለጫ

የስርዓተ ፆታና ታዳጊነት፡ አለማቀፋዊ መረጃ (ጌጅ) የጥናት ፕሮግራም ለዘጠኝ አመት (እ.ኤ.አ ከ2015 – 2024) የሚካሄድ ድብልቅ የረጅም ጊዜ ጥናት ሲሆን ከ10 – 19 ዕድሜ ያላቸው ታዳጊዎች በስርዓተ ፆታቸው አማካኝነት ስለሚያጋጥማቸው ህይወት የሚያጠና ፕሮግራም ነው። በአጠቃላይ የጥናት ፕሮግራሙ 20000 ታዳጊዎችን በስድስት ወኪል ሀገሮች ይከታተላል (ኢትዮጵያና ሩዋንዳ በአፍሪካ ፣ ባንግላዲሽና ኔፓል በኤዥያ እንዲሁም ጆርዳንና ሊባኖስ በመካከለኛው ምስራቅ እስያ)።

ጌጅ የታዳጊዎች ህይወት መሸጋገር በሚችልበት ጉዳይ ላይ መረጃ መፈለግ ዋናው ግቡ ሲሆን ይህም ታዳጊዎችን ከድህነትና መገለል ያላቅቃል፤ ፈጣን ማህበራዊ ለወጥም ያመጣል። ጌጅ በጥናቱ ያካተታቸው ተሳታፊዎች በጣም ተጋላጭ የሆኑ ታዳጊዎችን ሲሆን ታዳጊ ስደተኞችና ተፈናቃዮች ፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ያለእድሜ ያገቡና የወለዱት ዋነኞቹ ናቸዉ።

የጥናቱ ውጤት የፖሊሲ አውጭዎችና የፕሮግራም ፈጻሚዎች የአፍላ ወጣቶችን ህይወት እንዲያሻሽሉና ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ አቅም የሚፈጥር ሲሆን ይህም "ማንም ወደኋላ እንዳይቀር" (ሊቭ ኖ ዋን ቢሃይንድ) የሚለውን የአለማቀፍ ዘላቂ ልማት ግብ ለማሳካት ጉልህ ሚና ይኖረዋል።


የጌጅ ጥናት ጥምረት (GAGE consortium) በኦቨርሲስ ዴቨሎፕመንት ኢንስቲቱት (Overseas Development Institute (ODI)) የሚመራ ሲሆን 35 የሚሆኑ የጥናትና ምርምር ፣ የፖሊሲና ፕሮግራም ተባባሪ ተቋማትን አሰባስቦ የያዘ ነው ፤ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ደግሞ ከታላቋ ብሪታኒያ መንግስት ዩኬ ኤይድ (UK Aid) ነው።

## የፅንሰ ሀሳብ ንድፋችን

የጌጅ ጥናት የታዳጊዎችን አሁናዊም ሆነ የወደፊቱን እድገትና አቅም በሚገባ ለመረዳትና ለማዳበር ስለሚያስችል የሁለንተናዊ (Holistic) ፅንሰሀሳብ ንድፍን ይከተላል። በተለይም የታዳጊዎችን ሁለንተናዊ እድገት ለመቀየር ስርዓተ ፆታ ተኮር የአኗኗር ዘይቤ፤ አድሏዊ ልምዶችና ተግባሮች ከሌሎች ማህበራዊ ጉዳቶች ጋር ያለቸዉን ተዛምዶ ይዳስሳል።

- **አቅሞች** (Capabilities) - የታዳጊዎች ደህንነት መሰረት የሆኑ ግለሰባዊና ማህበራዊ አቅሞች ፤ ስድስት ዋና አቅሞችን (ትምህርትና መማር ፣ አካላዊ ምሉዕነት (ከፆታዊና ስርዓተ ፆታ ጥቃትና ያለእድሜ ጋብቻ ነፃ መሆን) ፣ የመራባት ጤንነትና ስነ-ምግብ ፣ የስነ ልቦና ደህንነት ፣ ድምጽና ውሳኔ ሰጭነት እና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት) የሚገዳደሩ ሁኔታዎችና መፍትሄዎች፤
- **የለዉጥ መንገዶች** (Change Strategies) - ሁለንተናዊ ለዉጥን ለማምጣት ተከታታይ የሆነ እርምጃዎችን በግለሰብ ፣ በቤተሰብ ፣ በማህበረሰብ ፣ በአገልግሎቶችና በተቋም ደረጃ የሚታቀዱ መንገዶች፡
- **ሁኔታዎች** (Contexts) - የአፍላ ወጣቶች እድገት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ አካባቢያዊ ፣ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ ሁኔታዎች፡

## የጌጅ ፅንሰ ሀሳብ ንድፍ



# የጥናታችን ጥያቄዎች

ከፅንሰሀሳብ ንድፉ ላይ በመነሳት ጌጅ የሚከተሉት ዋና ዋና ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል።

1. **በዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው የተለያዩ ሀገሮች ዉስጥ የሚኖሩ ታዳጊዎች ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት እንዴት ይሸጋገራሉ?**
- የታዳጊዎች ተሞክሮና ኑሮ ከእድሜ፣ አካል ጉዳትና አካባቢ ሁኔታ አኳያ እንዴት ይለያያል?
- የታዳጊዎች ህይወትና ተሞክሮ ከስርዓተ ፆታ አንጻር ምን ይመስላል? ታዳጊዎች የስርዓተ ፆታ ልማድና አድሏዊ እሳቤን እንዴት ይመለከቱታል?
- ወላጆች፣ ቤተሰቦች፣ ማህበረሰብ፣ አገልግሎት ሰጪዎችና ሚድያው  በአፍላ ወጣቶች ህይወት ላይ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው?
- ታዳጊዎች በአካባቢያቸው ስለሚያገኙ አገልግሎTOCEና ስርዓት ዙሪያ ምን ያስባሉ?
- ተቋማት፣ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች በአፍላ ወጣቶች ህይወት ላይ የሚጫወተት ሚና ምንድን ነው?

2. **ታዳጊ ተኮር የሆኑ የፕሮግራም ትግበራዎች ምን ተፅዕኖ አላቸው?**
- በታዳጊዎች አቅሞች ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች የሚኖራቸው የአጭርና ረጅም ጊዜ ተፅዕኖ ምንድን ነው?
- ፕሮግራሞች በቤተሰብ፣ አቻ እና  ማህበረሰብ አመለካከት፣ ተግባርና ልማድ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ምንድን ነው?
- የአፍላ ተኮር ፕሮግራሞች ከተዛማች አገልግሎቶችና ስርዓቶች ጋር (ለምሳሌ ጤና፣ ትምህርት፣ ፍትህና የህጻናትና ማህበራዊ ጥበቃ) እንዴት ይጣመራል?

3. **የፕሮግራም ቀረፃዎችና ትግበራዎች ባህርያት ምንድን ነው?**
- የፕሮግራሞች ይዘት፣ መዋቅርና ቅደም ተከተል የታዳጊዎችን ህይወት ምን ያህል ይለውጣል?
- የፕሮግራሞች ትግበራ ጊዜ በታዳጊዎች ሁለንተናዊ እድገት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ምን ያህል ወሳኝ ነው?
- የፕሮግራሞች ጥልቀትና  የትግበራ ጊዜ ምን ያህል ወሳኝ ነው?
- የፕሮግራም ግብዓቶች (በጀት፣ የሰው ሀይልና መሰረተ ልማት) ምን ያህል አፍላ ወጣቶችን ያማከሉ ናቸው?

# ጌጅ በኢትዮጵያ

የጌጅ ጥናት በኢትዮጵያ በጣም ተጋለጭ የሆኑ ታዳጊዎችን ለምሳሌ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዎችን (IDPs)፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ ከትምህርት ገበታ ውጭ የሆኑትን፣ ያገቡና የወለዱ ታዳጊዎችን እንዲሁም አርብቶ አደር ታዳጊዎችነ  ያካትታል። በነዚህ ተጋላጭ በሆኑ ታዳጊዎቸ ህይዎት ዙሪያ ያሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ተግዳሮቶችን ቀጣይ በሆነ መልኩ ከማጥናት  በተጨማሪ፣ የተጋላጭ ታዳጊዎችን በተለይም የህጻናት ጋብቻና የግርዛት አደጋ የተጋረጠባቸውን የታዳጊዎች ህይወት በማስረጃ ለመደገፍ ጌጅ ከሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሞ በመስራት ላይ ይገኛል። ጌጅ ከፓዝፋይንደር (Pathfinder ) እና ኬር ኢትዮጵያ (Care Ethiopia) ጋር በመተባበር አብረናት እንተግብር ኢትዮጵያ (Act With Her-Ethiopia) የሚባለው የትግበረ ፕሮግራም በተጋላጭ የገጠር ማህበረሰብ ደህንነትና ተጠቃሚነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ይገመግማል ። የአብረናት እንተግብር ኢትዮጵያ ፕሮግራም የሁለት አመት ዘርፈ-ብዙ ፕሮግራም ሲሆን ፈንድ የተደረገው በቢል እና ሚሊንዳ ጌትስ (Bill and Melinda Gates) ፋውንዴሽን ነው። የአብረናት እንተግብር ኢትዮጵያ ፕሮግራም ስርዓተ-ትምህርት ተኮር ፕሮግራም ሲሆን አላማውም የስርዓተ ፆታ ልማድን መለወጥ፣ ትንንሽ ሴትና ወንድ ታዳጊዎችን ማብቃት፣ ማህበረሰብ አቀፍ ተሳትፎና ስርዓትን ማጠናከር እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍን ያካትታል። በኢትዮጵያ በሶስት ክልሎች ውስጥ በሚገኙ ሶስት ዞኖች ማለትም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን፣ በአማራ ክልል ደቡብ ጎነደር ዞን፣ እና በአፋር ክልል ዞን አምስት እንሰራለን። ከዚህ በተጨማሪም በከተሞች ማለትም በድሬዳዋ፣ ደብረ ታቦርና ባቱ ከተማ አስተዳደሮችም የጥናት እና ምርምር ስራዎችን እንሰራለን።  በኢትጵያ የመጠናዊ ጥናታችንን ከላተራይት አለማቀፍ የጥናት ተቋም (Laterite Ltd) ጋር፣ የአይነታዊ ጥናታችንና ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚሰሩ  ስራዎችን ከኩዌስት የጥናት፣ ስልጠናና የማማከር ተቋም (Quest, Research, Training and Consultancy) ጋር እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከሌሎች የግል አጥኚዎች ጋር በትብብር በመስራት ላይ እንገኛለን።

# የጥናቱ ዘዴ

ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ ጌጅ ድብልቅ የጥናት ዘዴና የተፅዕኖ ግምገማ በትግበራና ከትግበራ ውጭ የሆኑ የጥናት አካባቢዎች ላይ ይተገብራል።

**አለም አቀፍ: 20,000**
**ኢትዮጵያ: 7,500**



**መጠናዊ ጥናት**
- ከ10 – 12 እና ከ15 – 17 እድሜ ያላቸው አፍላ ወጣቶች የሚካሄድ ጥናት
- ሴትና ወንድ አሳዳጊዎች ጋር የሚካሄድ ጥናት
- የማህበረሰብና ሀላፊዎችና የትምህርት ቤት ሰዎች

**800**
**250**



**አይነታዊ ጥናት**
- ከትትል የሚደረግባቸው ዋና ተጠኝ አፍላ ወጣቶች፣ እህትና ወንድሞቻቸው፣ አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ መሪዎች ጋር የሚደረግ ጥልቅ ቃለ መጠይቅ
- የዋና ተጠየቅ ቃለ መጠይቅ እና የታሪካዊ ሂደት ጥናት
- የፖሊሲ ፖለቲካና የፕሮግራም ትግበራን ለመረዳት የፖሊሲና የህግ ትንተና

**200**
**100**



**አመታዊ ኣሳታፊ ጥናት**
- የአፍላ ወጣቶችን አቅሞች በጊዜ ሂደት ለመለወጥ የአቻ ጥናትና አሳታፊ ፎቶግራፍ ተኮር ጥናት ከአቻዎቻቸው ጋር ማካሄድ
- የአቻ ግንኙነቶች በህይወታቸው ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ለመረዳት የማህበራዊ ጥምረት ትንተና ማካሄድ


**የበለጠ መረጃ በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል**

GAGE website
www.gage.odi.org

Twitter
@GAGE_programme

Facebook
www.facebook.com/GenderandAdolescence/

Email
gage@odi.org.uk

Cover photo: © Nathalie Bertrams/GAGE

ISBN: 978-1-912942-89-3

UKaid from the British people